ማርያሙ ልክ እያስገባህ ዝለቅ ቀጥለህ ከአዳም ፋሲካሁ ዕቀብኒ በተአምርኪን ወእድኅንኒ ከእሑድ መልክአ ውዳሴ ውስጥ አንቲን ብለህ በማያያዝ ሰአሊ ለነ ሰአሊ ለነ ማርያም እሙ ወእሙ ለእግዚእነ ወመዋርስቲሁ ደረስየን በየማኅ ታቦት ዊት ከሁለት አንዱን መርጠህ ይብል ዓብድ በልቡ ፪ኛ እግዚአ ሚ በዝሁትን ዝለቅ ስብሐት ሳትል በአቡነ ዘበሰማያት አሠር ይህ ድ ጋም ለጠላት መከላከያ ይሆናል፡ በተጨማሪ ፲፱ቱን መቃብያ ኖች ድገም የሚደገምበት መንፈቀ ሌሊት ከሰው ጋር ሳትነጋገር ከማንኛውም ሽንት ቤት ከመጠቀምህ በፊት ድገም። ስለ መል ክአ ኖላዊ በውሃ ላይ መልክአ ኖላዊን ስትደግም ሰንብተህ አርብና ረብሁ ተጠመቅ። በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ጸሎት በእንተ ዐቃቤ ርእስ ዘጸለየ ዳዊት ምስለ ሕሊኣሁ ሳዶር አላዶር ዳናት አዴራ ሮዳስ ጸጋ ዘአብ ማዕተብ ዘወልድ ዘተውህበ ለኢሕዛብ ይኩኖ ረዳኤ ወዐቃቤ ወመድኅን ፈልፈለ ጥበብ በዠሉ ፍኖትየ ኀበ ሖርኩ በምሥራቅ ወበምዕራብ በሰሜን ወበደቡብ አብ ይሰመይ ታዖስ ወልድ ይሰመይ ታዖስ መንፈስ ቅዱስ ይሰመይ ታዖስ ስሙ ለአብ ሙራኤል ስሙ ለወልድ ምናቴር ስሙ ለመንፈስ ቅዱስ አብዮቴር ስሙ ለአብ ቡሩክ ፉሲሞልደስ ስሙ ለወልድ ዋህድ ዡርዡርያኖስ ስሙ ለመንፈስ ቅዱስ ማኅየዊ ጢኖጢቃኖስ ዝንቱ አስማተ መንፈስ ቅዱስ ይኩኖ ረዳኤ ወዓቃቤ ወመድኅን በሥጋ ወነፍስ ማር ጊዮርጊስ መዋዒ ሰማዕቱ ለኢየሱስ ክርስቶስ በቤት ወበገዳም በባሕር ወበየብስ ዕቀበኒ እመከራ ሥጋ ወነፍስ ሊተ ለገ፡ ዕገሌ ለማንኛችውም ነገር ጠዋት በጠዋት ስትነሳ ፲፲ ጊዜ ደግመህ ሂድ

እመልክኢሆሙ ለኢሕዛብ ዘወርቅ ወዘብሩር ሽረክ ፫ ጊዜ ግብረ ዕደ ዕጓለ እመሕያው ወለአብትር ፫ ጊዜ አፍ ቦሙ ወኢይነቡ ፍሎሙ ፫ ጊዜ ዓይነ ቦሙ ወኢይሬእዩ አእእእ እያል ፫ ጊዜ ዕዝነ ቦሙ ወኢይሰምዑ ሞአኒል ፫ ጊዜ እንፍ፡ ቦሙ ወኢያጼንዉ ሉአሊል፫ ጊዜ ዕደ ቦሙ ወኢይ

ገሡ ወዲ ፫ ጊዜ እግር ቦሙ ወኢየሐውሩ ድርሞኒ ፫ ጊዜ ወኢይነቡ በጕራዒቶሙ እስመ ሣረራ ፫ ጊዜ ወእልቦ መንፈስ ውስተ አፉሆሙ በገዛ ቃለ ዳዊት ወበዝ ቃለ ዓረቢ ከማሆሙ ለይኩኑ እለ ገብርዎሙ እፍገዘዞሙ ወእቅዝዞሙ ለኵሎሙ ፀርየ ወጸላእትየ ወኵሎሙ ውሉደ አዳም ወሔዋን ሊተ ለገብርከ ዕገሌ። **ገቢር** በዕለት ሌሊት ውሃ ላይ ፯ ጊዜ ደግመህ ጾም ካልሆነ ፋት ብሉ መጉንጩት ጾም ከሆነ ፊትን መታጠብ ነው **ለፀር መዝ፡ ፭ ፍኪሬን** ሌሊት ሣይነጋገሩ ማንኛውንም ሽንት ቤት ሳይጠቀሙ በጎቡዕ ፯ ጊዜ መብራት እያጠፉ እያበሩ መድገም ነው።

**ለስቃቤ ርእስ** መዝሙር ፭ ቃልየ አጽምዕን በየብስም በባሕርም በመንገድም እህል ሳትቀምስ በቅብዐ ቅዱስ በሜሮን ውሃ ባልነካው ቅቤ በማንኛውም ቅባት ላይ ፯ ጊዜ ደግመህ ተቀባ ከሞት ይጠብቅሃል። ዓዲ ለራስ ምታትም በቅቤ ፯ ጊዜ ደግመህ ተቀባ፡


**ዓይኑን ለታመመ** መዝሙር ፮ እግዚኦ በመዓትከ ኢትቅሰፈኒ ወተሐውከት እመዓት ዓይንየ አለው ድረስ ጽፈሕ አሲዘው በቅቤም ፯ ጊዜ ደግመህ ቀባው ይድናል ደግሞም ለምትፈራው ነገር ሁሉ ከቤት ሳትወጣ ማንኛውንም ሺንት ቤት ሳትጠቀም ከሰው ሳትነጋገር የምትፈራውን ሰው ስም ከነእናቱ ስም እየጠራህ ፯ ጊዜ ድገም ከእሱ ትድናለህ።

**እስማት ለተሞሰበትና የኢጋንንት ቁራኛ ለያዘው ሰው** መዝሙር ፯ እግዚኦ አምላኪየ ብከ ተወከልኩን ፀሐይ ከማታየው ጉድጓድ ውኃ ቀድተህ ፰ ቀን ፯ ፯ ጊዜ ደግመህ አጥምቀው **በእግዚአብሔር** ቸርነት ይድናል ይህንንም ስታደርግ ልጅና ከብት ማንኛውም ሰው ከሌለበት ሜዳ ነው ከቤትም ከመንገድም አትድገም። ዓዲ ባላ ለጠላት ሴት በቅቤ ፯ ጊዜ ደግመህ ሰውነቷን ትቀባ ።


**ለታመመ ሕፃናት** መዝ፡ ፰ እግዚኦ እግዚእነን ጽፈህ አሲዝ ይፈወሳሉ። ለታሠረ ሰውም በጎብስት ላይ ጽፈህ

ስጠው **በእግዚአብሔር** ቸርነት ይፈታል ዓዲ በዝርግ ሳህን ላይ ጽፈህ በዓሣ መረብ ከተህ ከባሕር ብትጥለው ብዙ ዓሣ ይያዝልሃል። ዓዲ ለገበያ በእንግሬሎ እርጩሜ ፯ ጊዜ ደግመህ የምትሸ ጠውን ዕቃ ፯ ጊዜ ብትመታው ይሸጣል። ዓዲ ጥሬ ጨው በማር ለውሰህ ፯ ጊዜ ደግመህ ብትበላ ከሰው ጋር በፍቅርና በሰላም ለመኖር ያስችልሃል።

**ጠላትህ በበረታብህ ጊዜ መዝ፡ ፶ እግኒ ለከን** የራሱንና የአ ሀገር ቢጠላህ ፯ ጊዜ በሌሊት ውሃ ደግመህ በ፴ቱ ማዕዘን እርጭ። ዓዲ ሰው በታመመብህ ጊዜ እነዚህን ጠልሰሞች በአዲስ ሸክላ ላይ ጠልስመህ የጽጌ ረዳ ውሃ ጨምቀህ በው ሃው አጥበህ ይህንኑ መዝ፡ ፫ ጊዜ ደግመህ በሽተኛውን ብትቀባው በእግዚአብሔር ቸርነት ይድናል።




መዝ፡ ፲ን ጽፈሕ ብትይዘው ሰው ሁሉ አይናገርህም።
መዝ፡ ፲፩ አድኅነኒ እግዚኦን ከነጠልሰሙ ጽፍ በጽፈቱ ላይ ፫ ጊዜ ደግሞ ቢይዙት በሰው ዘንድ ክብርና ልዕልና ይሆናል።



ዓዲ በ፯ቱ ቀሰማት ጽፈሕ በክንድህ ብትይዘው ከክፉ ሰውና ከቅዠት ሕልም ያድንሃል።

መዝ፡ ፲፪ እስከ ማዕዜኑን ለዓይን ሕመም አብርሆን ለአዕይንትየ ከመ ኢይኑማ ለመዊት አለው ድረስ ጽፈህ አሲዘህ በዘይት ፯ ጊዜ ደግመህ ቅባው፡ ወይም በውሃ ፯ ጊዜ ደግመህ ዕጠበው። **ዓዲ** በሐዲስ ዕቃ ላይ ጽፈህ በቅብዓ ቅዱስ ጽሕፈቱን አጥፍተህ ብልቱ ለሞተበት ሰው ቅባው ይፈታለታል። **ዓዲ** ስትተኛ ፫ ጊዜ ብትደግመው

ከሌባ ከጠላት ይጠብቅሃል:: መዝ: ፲፫ ይብል አብድ በልቡን በጥሬ ጨዉና በውሃ ፯ ጊዜ ደግመህ በዕቱ ማዕዘን ብትረጨው ጠላትህ ይታገስልሃል:: ልጅህን ወደ ተማሪ ቤት ወይም ወደ ሥራ ቦታ ልትሰደው ብታስብ በአንድ መስኪያ መጠጥ ላይ ፫ ጊዜ ከደገምህ በኋላ በአዲስ ሸክላ መዝሙሩን ጽፈህ በደገምህበት ውሃ ጽሑፉን ቅጥበህ እጣቢውን ከማሠሮው ገልብጠህ ውሃ ሞልተህ ማሠሮውን ያደስ ቅጠል ወትፈህ ከማንኛውም ነገር ንጹሕ ሆነህ ፯ ቀን ፯ ፯ ጊዜ ደግመህ በ፫ኛው ቀን አጥምቀኸው ወደ አሰብከው ቦታ ስደደው ማንኛውም ነገር ይቃናለታል መዝ: ፲፬ እግዚኦ መኑ የኀድርን ወደ አዳራ ወይም ሽንት ቤት ሳትወጣ በቅብዓ ቅዱስ ፫ ፫ ጊዜ እስከ ፯ ቀን ደግመህ በ፫ኛው ቀን ተቀባ ልዕልና ታገኛለህ መዝ: ፲፭ እግዚኦ ስምዓኒ ጽድቅየን ከመንግሥትም ቤት ከጳጳሳትም ቤት ከዳኛም ቤት ነገር ቢኖርብህም ፲፲ ጊዜ ድገም በእግዚአብሔር ስም አድርገህ ትመጣለህ ዓዲ ጠላትህን በአንተና በእሱ ስም እየጠራህ ብትደግም ጠላትህ ይታገስልሃል ዓዲ ለታመመ ሰው በአዲስ ዕቃ ፀሐይና ጨረቃ ከማይደርሱበት ቦታ ውሃ ቀድተህ በውሃው ላይ ፲፪ ጊዜ ደግመህ መዝሙሩን ከጠልስመ- ጽፈህ ካስያዝከው በኋላ ብታጠምቀው ፈጥኖ ይፈወሳል ::




መዝሙር ፲፯ አፈቅረከን ወተኃስሮሙ ለአዕይንተ ዕቡያን እስኪል ድረስ በግራ ጉንህ ጽፈህ ያዝ፡ ከዚያ በላይ ያለው በቀኝ ጉንህ ያዝ፡፡ ከክፉ ነገር ከጠላት ይሠውርሃል፡፡ ዓዲ በጥርኝ አፈር ሕዝብ ዘኢየአምር ተቀንየ ሊተ እስኪል ደግመህ አፈሩን እርጭ እግዚአብሔር ከእጃቸው ያድንሃል።

ዓዲ ለታቦት አህል ሳትቀምስ በማየ ኢ.ጺ.ፋንያ ደግመህ ተሐጸብ።

መዝሙር ፲፰ ለማያት ይነግራን ሕፃናት እንዳይደነግጡ በልብሳ ቸው ወበአቂቦቱ ይትሐሠይ ብዙኃ እስኪል ፫ ጊዜ ድገም። ዓዲ ለወሊድ በውሃና በመጠጥ ነገር ይህን መዝሙር መላውን ፫ ጊዜ ደግመህ አጠጣት እግዚአብሔር ይምራታል። ዓዲ ለሴባ ዕቀበኒና ይስማዕከን ብትደግም ይከላከልልሃል። መዝሙር ፲፱ ይስማዕከን ከመንግሥት ከመኳንንት ቤት ስትገባ መላውን ጽፈህ ሙስተካ ዕጣን አጥነህ ያዝ በቅብዐ ቅዱስም ወንትፌሣሕ በአድኅኖትከ እስከሚለው ድረስ እየደገምህ ተቀባ። ዓዲ ለአበደ ሰው እንደ ትእዛዝ ባለ ወረቀት ከነጠል ሰሞቹ ጽፈህ ጽፈቱን በማር ብርዝ አጥበህ የማርያም ቅጠል ጨምረህ አጠጣው ቀባው በእግዚአብሔር ቸርነት ይድናል።




እኒህን ጠልሰሞቹን በስንዴ ቂጣ ጽፎ መዝሙሩን በላዩ ደግሞ ይይዟል። ለታሠረ ሰውም እንዲሁ አድርጎ ቢያበሉ ከጸበሉም ቢጠጣ ፈጥኖ ይፈታል። ለአበደ ሰው መዝ ፳ እግዚአ በኃይልከ በጠርሙስ ላይ ጽፈህ በብርዝ አጥበህ የደረኩስ ቅጠልና የማርያም ቅጠል ጨምረህ አጠጣ በእግዚአብሔር ቸርነት ይድናል ዓዲ በወረ ቀት ጽፈህ ሙስቲካ ዕጣን አጥነህ ያዝ ልዕልና ይሆንልሃል። ለወሳድ መዝ፡ ፳፩ አምላኪየ ጽፈህ በላይዋ ላይ አዙረህ ጣል፡ ዓዲ ለበግና ለቅዱስ ከብት ጽፎ ቢያሲዙት አውሬ አያስነካም ወይም ለአይነተኛው ከብት ቢያስሩት ሌሎችንም ይጠብቃል። ዓዲ እስመ አንተ እውጻእከኒ እምከርሥ እስኪል ጽፎ በመጠጥ አጥበህ መላ መዝሙሩን ፫ ጊዜ ደግመህ አጠጣ አብሮ የሚጻፉ ጠልሰችም እኒህ ናቸው።




ለታሠረ ሰው መዝ፡ ፳፪ እግዚአብሔር ይሬእየኒ ጽፎ ቢያስዙት ይፈታል። ዓዲ እህል ስትዘራ በሮት እፍኝ እህሉ ፫ ጊዜ ደግመህ ከዘሩ ጨምረህ ዝራ በእግዚአብሔር ቸር

በረከት ይገኛል ዓዲ በውሃና በጥሬ ጨው በጥብጠህ ጠል ሰሞቹን ጨምረህ በውኃው በጥብጠህ በቤትህ ዙርያ እርጭ




መዝ፡ ፳፫ ለእግዚአብሔር ምድር በምልዓን መኑ ውእቱ ንጉሠ ስብሐት እስከሚለው ድረስ ከነጠልስሙ ጽፈህ በ፩ቱ ማዕዘን ከቤትህ ስቀል አራዊት ወደ ቤትህ አይቀርቡም።




ዓዲ መክፈቻ ቢጠፋብህ በንጽሕ ሆነህ ፯ ጊዜ ብትደግም ይከፈትልሃል። ዓዲ ክፉም ሆነ በጐ ለማየት በንጹሕ ሆና እግዚአብሔርን በራዕይ ልጠይቅ ላለ ሰው በሚተኛበት ጊዜ የተለመደውን ጸሎቱን ከጨረሰ በኋላ ይህን መዝሙር ፯ ጊዜ ደግሞ ቢተኛ ያሰበውን ሁሉ እግዚአብሔር ይገልጽለታል፡ ሕልመ ዮሴፍ ማለት ነው። መዝ፡ ፳፬ ኀቤከ እግዚኦ እንቃዕዶኩን የዓውደ ዓመቱ ቅዱስ ዮሐንስ ዕለት ጨው በውሃ በጥብጠህ በላዩ ፯ ጊዜ ደግመህ በቤትህ ዙርያ ብትረጨው ከዓመት እስከ ዓመት ሲሳይ ይገባልሃል ዓዲ መዝሙር ፳፬ና ፳፯ ዘወትር ለሚጸልይባቸው ብዙ ጥቅም አላቸው የኃጢአት መደምሰሻና የሥጋ መጠገኛ ይሆናሉ፡ ዓዲ ውጋትና ቁርጥማት ለሚያመው ሰው በሐዲስ መርፌ የነጭ ሐር ክር አድርገህ ፳፩ ጊዜ ድገም በደገምህ ቁጥር የሐሩን ክር ቋጥር መርፌውንና ፈትሉን በሴት ወፍ ደም ነክረህ በመርፌው የሕመምተኛውን ሰውነት ብትወጋ ከበሽታው ይፈወሳል ዓዲ በቤትህም ሆነ በሌላ ሰው ቤት የሚያስፈራ ነገር ቢኖር ፯ ቀን ፯ ፯ ጊዜ ብትደግም ችግሩ በእግዚአብሔር ቸርነት ይወገዳል ዓይኑን ለታመመ ሰው መዝ፡ ፳፭ ፍታህ ሊተን በሆነ ዕቃ ላይ ጽፈህ ጽሕፈቱን በውኃ አጥበህ ፯ ጊዜ ደግመህ ዓይኑን ብታጥበው ይድናል ዓዲ ወደ

ምትፈራው ነገር ስትሄድና ወደ ሹም ቤት ስትሄድ በጽጌ ረዳ አበባ ቅባት ፯ ጊዜ ደግመህ ብትቀባ በደህና ትመለሳለህ ዓዲ ከነዚህ ጠልሰሞች ጋር መላውን ጽፈህ በቀኝ ጎንህ ብትይዘው ከክፉ ያድንሃል በሰው ዘንድም ክብር ታገኛለህ።



መዝ፡ ፲፱ እግዚአብሔር ያበርህን ወደ ንጉሥና ወደ ሹም ቤት እንዲሁም ወደ መንገድ ለመሄድ ከቤትህ ስትወጣ ፫ ፫ ጊዜ ድገም በሰላም ትመለሳለህ ዓዲ ሌባ ዕቃህን ቢሰርቅብህ መዝሙሩን ፯ ጊዜ ደግመህ ሰርቆኛል ብለህ በጠረጠርከው ሰው ስም የዕገሌን ልጅ ዕገሌን በዕገሌ ቀን የሠረቀውን እንደዚህ ድፈነው ብለህ የጻፍከውን ጽሑፍ ቅበር ካልመለሰ አታውጣው የወሰደውን እንዲመልስ ያስገድደዋል የምትጠላው ሰው እንዳይመጣብህ ብትፈልግ መዝ፡ ፳፯ ኀቤከ እግዚኦ ጸራሕኩ በሰውየው ስም ፯ ጊዜ ብትደግም ይመለሳል ዓዲ ፀመንፈስ ርኩስ ለታመመ ሰው ፀሐይ ከማትደርስበት ጉድጓድ በሐዲስ ጽዋዕ ውኃ ቀድተህ ከአጭሩ ካላፈራው ጽጌ ረዳ ፯ ቅጠል በተራው ፬ ቀንበጥ አምጥተህ ከውሃው ጨምረህ እስከ ፫ ቀን ፯ ፯ ጊዜ ደግመህ ብታጠምቀው ይድናል ሙሉ መዝሙሩን ከነጠልሰሙ ጽፈህ አስይዘው ዑድ ሙስተካ ዕጣንም ዕጠነው፡ ዓዲ ሐዲስ ቤት ለመስራት ብትፈልግ በሐዲስ ዕቃ ውኃ አድርገህ ወቦቱ ተወከለ ልብየ ወይረድአኒ እስከሚለው ድረስ ፯ ቀን ፯ ፯ ጊዜ ደግመህ ጠልሰሞቹን ጽፈህ ጽሑፉን ሕጥር የሚባል ሽቶና ዕፀ ፋርስ አጥንህ ቅበርበት ክፉ ነገርና ጥፋት አይደርስበትም።




ለህብት ለሲሳይ መዝ፡ ፳፰ አምጽኡ ለእግዚአብሔር

በወንድ ፍየል ጥፍር ጽፈህ በዓውደ ዓመቱ ቅዱስ ዮሐንስ


ዕለት በሐዲስ ዕቃ ውኃ ቀድተህ ከዚያ ጽሑፉን አግብተህ ጨው ጨምረህ ቤትህን ብትረጨው ይሆናል። ዓዲ ከጽጌ ረዳም ከዘይትም ጋራ ደግመህ ለበሽተኛ ብትቀባው ይፈወሳል ዓዲ በውኃ ደግመህ እንቅልፍ ለከሰከሰው ብታጠጣው ይድናል ለህብትና ለሲሳይም ይበጃል ጥሩ ነው ።

በክፉ ለሚያስብህ መዝ ፳፱ እአዙተከን በእናቱና በእሱ ስም እየጨመርክ ፯ ቀን ፯ ፯ ጊዜ ብትደግም እግዚአብሔር ጠላትህን ያስታግስልሃል ዓዲ ብልቱ ለሞተበት ከነጠልሰሙ ጽፎ ይዞ ፫ ፫ ጊዜ ጠዋትና ማታ ቢደግም ይፈወሳል።



ሌሊት ለማባንን መዝ፡ ፴ ኪያከ ተወከልኩን በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ አስይዘው። ዓዲ በጠላህ ሰው በስሙ እስከ እናቱ ስም እስከ ፫ ቀን ፫ ፫ ጊዜ ብትደግም ይታገሣል ዓዲ ክፉን ነገር ለማራቅና የልብ በሽታን ለማስወገድ በተዘዋዋሪ በሰውም ሆነ በአጋንንት ነገር በክፉ ለሚያስብሕ ይህን መዝ፡ ብትደግም በእግዚአብሔር ቸርነት ጠላትህ ይታገሳል

ለአበየ ሰው መዝ፡ ፴፩ ብፁዓንን በጥር ውሃ ሎሚና በኩረ ሎሚ እየጨመርክ ፯ ጊዜ ደግመህ አጥምቀው መዝሙሩን ከነጠልሰሞቹ ጽፈህ በግራር ቅጠል አጥነህ አስይዘው ዳግም አይመለስበትም



ለኃይለኛና ለተንኰለኛ ማድከሚያ መዝ፡ ፴፪ ተፈሥሑ ጻድቃንን ከነጭ ልብስ ቅዳጅ ከለበስኸውም ቢሆን እንደ ትእምርተ መስቀል አድርገህ ቀደይ መዝሙሩን እግዚአብሔር ይመይጥ ምክሮሙ ለአሕዛብ እስኪል ድረስ ፯ ጊዜ ደግመህ ከሕገዘቡ መካከል ጣለው እግዚአብሔር ያዳክመዋል


## አጥንቱ ለተሰበረበትና ጥርሱን ለሚያመው ሰው መዝ፤ ፻፲፫

እባርኮን እግዚአብሔር የዓቅብ ኵሉ አዕጽምቲሆሙ ወኢ ይትቀጠቀጥ አሐዱ እምውስቴቶሙ እስከሚለው ድረስ ከነጠልሰሙ ጽፈህ መዝሙሩን መላውን ፯ ጊዜ ደግመህ ጽፈቱን በዘይት አጥበህ ጥርሱን ቅባው። አጥንቱንም ቅባው መዝሙሩ የሚጻፍበትን ዕቃ አስቀድመህ የምድር ዕንቧይ ፍሬ ውስጡን ዕጠነው በኋላ ጠልስምበት። ዓዲ ሰው በወንበዴ እጅ ቢወድቅ ፫ ጊዜ ድገም ጠልሰሞቹን በልቡ ያስባቸው።



በሰው ዘንድ ክብርና ልዕልና እንዲታገኝ ጠላትህ በክፋት ቢያስብህ እህል ሳትቀምስ መዝ፡ ፻፬ ግፍያሙን እስከ ፫ ቀን ፫ ፫ ጊዜ ድገም ከተኩለኛው ያወጣሃል ዓዲ ከማንም ብተጣላህ ጊዜ መዝሙሩን በልሙጥ ወረቅት ጽፈህ ይዘህ ከምትፈራው ስፍራ ስትሄድ ድገም ከዚያ ከክፉ ነገር ያወጣሃል


በንዳድ ለታመመ ሰው መዝ፡፻፳ ይነብብ ኃጥእን በዕቃ ጽፈህ በጥሩ ውኃ አጥበህ አጠጣው ቅባውም ለተሰበረ ሰውም ብታጠጣው ይድናል። ዓዲ ለበግና ለላምም ቢሆን ተከር እንዳይነካቸው ጽፈህ ከማደሪያቸው ከበረቱ ቅበር ዓዲ ብልቱ ለደከመበት ሰው ይህን መዝሙር ጠዋትና ማታ ፯ ፯ ጊዜ ይድገም ይድናል። ለክብርና ለልዕልና መዝ፡ ፻፮ ኢትቅናዕ ላዕለ እኩያንን ከነጠልሰሙ ጽፈህ ብትይዘው ለክብርና ለልዕልና ይሆናል፡ ዓዲ እያደር ምች ለሚጸናበት ሰው ጽፈህ እስይገዝ። ዓዲ ክፉም ሆነ በጐ በራእይ ለማየት ፯ ጊዜ ደግመህ ተኛ ዓዲ ጽፈህ ብትይዘው ለዓይነ ወርቅ ይሆናል፡ ዓዲ ለኃጢአት ማሥተስረያ ይሆናል፡ ዓዲ ለቁርፀት በ፩ መለኪያ ውኃ ደግመህ አጠጣው ይፈውሳል ዓዲ ለክብት ተከር (ትኩር) ጽፈህ በአውራው ዕሥር ይድናል ዓዲ ሴትን ብጠርጥር የምታደርገውን ለማወቅ ደግመህ ተኛ።




መዝ፡ ፴፯ እግዚኦ በመዓትከን ጽፈህ ከበግም ከላምም ቦታ አዙረህ ብትቀብረው ከአውሬ ይጠብቅልሀል ዓዲ ለታመመ ሰው በውኃ ደግመህ ብትሰጠው ይፈወሳል፡፡ ዓዲ ለዓይን ሕመም ከቅዳሴ ፀበል ጋር ፯ ጊዜ ደግመህ ዓይኑን ዕጠበው ዓዲ ጠልሰሞቹን ጽፈህ ለንድሮስና ሙስተካ አጥነህ ያዝ፡ ዓዲ ጭንቅ ነገር ቢያገኝህ ሌሊት በባዶ ሆድህ ድገም ከመከራ ያወጣሃል፡፡




ለጥርስ ሕመም መዝ፡ ፴፰ እቤ እእቅብን ጽፈህ ያዝ ዓዲ ለራዕይ ይህንን ፯ ጊዜ ደግመህ እግዚአብሔርን በእመ ብር ሃን ተማፅኛሃለሁ የፈለግሁትን አሳየኝ ብለህ ብትተኛ ያሳ ይሃል ከክፉ ለመሠወርያና ለጠላት ማስታገሻ መዝ፡ ፴፱ ጸኒሃ ጸናህኩም ሰው እንዳይጠላህ ይህን መዝሙር በወንድ ዶሮ ደም ጻፍና ያዝ በደጃፍህም ከነዚህ ጠልሰሞች ጋር ቅበር፡፡ ዓዲ ወደ ጉዳይህ ስትወጣ መሆኑንና አለመሆኑን ለማወቅ ከዚያ ቦታ ስትደርስ ቢሆን ፯ ጊዜ ባይሆን ፫ ጊዜ ድገም ያስታውቅሃል፡፡



መዝ፡ ፵ ብፁዕ ዘይሌቡን ሁል ጊዜ ብትደግም ከሰውና ከልሳን ሰብእ ያድንሃል፡፡ ዓዲ ለአቃቤ ርእስ ጽፈህ በቀኝህ ጎንህ ያዝ ከነገሥታት ከመኳንንት ዘንድ ብትሄድ ይቀናሃል፡ ዓዲ ጠላት ቢነሳብህ በጥርኝ አፈር ደግመህ በትንበት ይታገስልሀል፡ ከብት ቢጠፋብህ መዝ፡ ፵፩ ከመ ያፈቅርን ከጠልሰሞቹ ጋር በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ ተንተርሰህ ተኛ ሌባውን ያሳውቅሃል፡፡




ለሚፈራና ሌሊት ለሚባንንም ለሚቃዥም መዝ፡ ፵፪ ፍታሕ ሊተን ጽፎ ማስያዝ ነው ያድነዋል፡፡ ዓዲ ዓይኑ ለታመመ ሕመምተኛው እራሱ ጽፎ ይያዝ፡፡ ቁርፀት ለታመመም ሰው ጽፎ ከዕንብርቱ ማሠር ነው አባለ ዘሩ ለደከመ ሰው መዝ፡ ፵፮ ኵልክሙ አሕዛብን በዕቃ ላይ ጽፈህ በቅባት አጣፍጠህ ይቅባው የሴቲቱን ቀኝ እጇን ይዞ ወደ መኝታው ይሂድ ከሀገሩ ወጥቶ ለሄደና አልመለስም ላለ ሰው መዝ፡ ፵፯ ዓቢይ እግዚአብሔርን በመጀመሪያ በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ መስከና ጥንጁት ቅጠል አጥንህ ከነጠልሰሙ ከሸንበቆ አግብተህ በነፋስ ቦታ ስቀለው ይመለስልሃል፡፡



ዓዲ ሰውነቱ በፍጅት ወይም በትኩሳት ለሚታመም ሰው በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ አስይዝ፡፡ ዓዲ በወፍ ደም ከጻፍክ በኋላ ይዘህ ከሴት ብትሄድ አትደክምም ዓዲ ጠላት ሁል ጊዜ እያስፈራራ ቢያስጨንቅህ ጽፈህ ያዝ አዘውትረህም ድገም ይታገስልሃል፡፡

ሌባ በሠርቅህ መዝ፡ ፵፰ ስምዑ ዘንተን ከነጠልሰሙ ከሌባው ስም ጋር በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ በቀኝ ጉንህ ብትይዝ ሌባው ንብረትህን ይመልሳል፡፡



ወደ መንግሥት ወይም ወደ ማንኛውም ዳኛ መሥሪያ ቤት ስትሐየድ መዝ፡ ፵፱ አምላከ አማልክትን በመንገድ እየደገምክ ብትሄድ በሰላም ትመለሳለህ፡ ዓዲ ፍጅት ወይም ትኩሳት ወይም ቃር ላመመው ሰው በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ አስይዘው ዓዲ ለመካን ሴት በምንጣፏ ጻፍላት ትፀንሳለች፡



ሌሊት መንገድ ለሚሄድ ሰው እንዳይፈራ መዝ፡ ፺ ተሣ
ሃለኒን በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ አስይዘው፡፡ ዓዲ ለደመ
ነስርም በልሙጥ ወረቀት ጽፎ ቢይዙት ነስሩ ይቆማል፡፡

ለትኋንና በቤት ለሚለዋወሱ አራዊት ሁሉ መዝ፡፻፩ ለም
ንት ይዜኃርን በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ በቤትህ ብትሰቅሪ
ይጠፋሉ፡ ዓዲ ከሴት ጋር ተጣልተህ ወደ ዳኛ ብትሔድ ፫
ጊዜ ደግመህ ብትሄድ ይቀናሃል፡፡


ከሰው ጋር ጉዳይ ኖሮህ ከቤትህ ስትወጣ መዝ፡፻፪ ይብል
አብድን ፯ ጊዜ ብትደግም የኃይለኞችንና የክፉዎችን ጉል
በት ያደክምልሃል፡፡ የምትፈራውንም ያስቀርልሃል፡፡

ከቤትህ ወጥተህ መንገድ ለመሄድ ብታስብ መዝ፡ ፻፫ እግ
ዚኦ በስምከ አድኅንኒን እየደገምህ ብትሄድ ወደ ቤትህ በሰ
ላም ትመለሳለህ፡ ዓዲ ብትንሽ ዓሣ ፯ ጊዜ ደግመህ በመረቡ
ብታሥር ብዙ ዓሣ ይያዛል ለአጋንንትም ብትደግም ይሸሻሉ

ከማንኛውም ሰው ጋር በሰላም ለመኖር መዝ፡ ፻፬ ስምአኒ እግ
ዚኦ ጸሎትየን ጧት ጧት ፫ ፫ ጊዜ ብትደግም በሰላም ትኖራለህ፡


ለበሽተኛ ሰው መዝ፡ ፻፭ ተሣሃለኒ እግዚኦ እስመ ኪያከን
በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ ብታሲዘው ይድናል፡፡

ፍልፀትና ቁራኛ ለማያመው ሰው መዝ፡ ፻፮ ተሠሃለኒ እግዚኦ
ተሣሃለኒን በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ ብታሲዘው
ይድናል፡፡ ዓዲ በዕቃ ላይ መዝሙሩን ከጠልሰሙ ጋር ጽፈህ
በውኃ አጥበህ ቤትህን ብትረጨው ለሲሳይ ይሆንሀል፡፡



ከመንግሥት ቤት ስትገባና ለንግድ መዝ፡ ፻፯ አመሰ አማ

ጓን በልሙጥ ወረቀት ከጠልሰሙ ጋራ ጽፈህ በጥንጁትና በሙስተካ ዕጣን አጥንህ ብትይዝ ለክብርና ለልዕልና ይሆናል።




ለጠላት መዝ፡ ፶፰ አድኅነኒ እግዚኦ እምፀርየን በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ ብትይዝ ከክፉ ነገር ትድናለህ። ዓዲ ሴት ከባሏ ፈቃድ ስትወጣ ድንገት ቢጠራጠራትም በል ሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ አስይዛት ባሏ ይታረ ቃታል አይጠረጥራትም። ዓዲ በፍልፀት ወይም በምች ቢታ መም በልሙጥ ወረቀት ጽፎ ፯ ጊዜ ደግሞ በእራሱ ቢይዝ ከሕ መሙ ይድናል ዓዲ ወደ ማንኛውም ቦታ ስትሔድ በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ ብትይዝ በሰላም ትመለሳለህ።

ለዐቃቤ ርእስ መዝ፡ ፶፱ እግዚኦ ገደፍከነን በልሙጥ ወረ ቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ ብትይዝ ከበረሃም ከመንገድም በእግዚአብሔር ቸርነት ይጠብቅሃል። ዳግም ወደ ምትፈ ራው ስትወጣ ከቤትህ ፯ ጊዜ ደግመህ ብትወጣ ከክፉ ነገር ያድንሃል። ዳግም ለታሠረ ሰው በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ ብትሰጠው እግዚአብሔር ከመከራ ያወጣ ዋል። ዳግም ዘወትር ፴ ፴ ጊዜ ብትደግም ኃጢአትህ ይሠረይልሃል ዳግም በባህርና በየብስ በበረሃም ስትሔድ ፲፲ ጊዜ ደግመህ በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ በአንገትህ ብታንጠለጥለው ሰው ሁሉ ያከብርሃል።።

ወደ ማንኛውም ጉዳይህ ስትሔድ መዝ፡ ፷ ስምአኒ እም ላኪየ ስዕለትየን ፫ ጊዜ ብትደግም ይቀናሃል ዓዲ በመለኪያ መጠጥ ፫ ጊ!ዜ ደግመህ ብትጠጣው ሰው ሁሉ ይወድሃል፡


ወደ መንገድ በወጣህ ጊዜ መዝ፡ ፷፩ አኮኑ ለእግዚአብሔርን ፯ ጊዜ ብትደግም ከፍርሃት ከምንኛውም ነገር ትድናለህ፡ ዓዲ

በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ በውኃ አጥበህ ለአት
ክልት ብትረጨው ከክፉ በላተኛ አዝመራውን ይጠብቀዋል።
ወደ ጉዳይህ ወይም ወደ ሹም ቤት ስትሔድ መዝ፡ ፷፱
እምላኪየ አም፡ እንይስን ፯ ጊዜ ደግመህ ሒድ ሲሳይ ታገኛለህ




የታመመ ውሻ ለነከሰው ሰው መዝ፡ ፻፩ ስምአኒ እግዚኦ
ጸሎትየን በአንድ ብርሌ ጠጅ ፯ ጊዜ ደግመህ ብታጠጣው
በእግዚአብሔር ቸርነት ይድናል።
ለሱቃይና ለበረከት መዝ፡ ፷፬ ለከ ይደሉን በዓረብ ቋንቋ
ሸሸህርላዳክ በምትባል ዕንጨት በዕቃ ላይ ጽፈህ ጽሑፉን
በውኃ አጥበህ በሱቃያውም ሆነ በቤትህ ብትረጭ በእግዚ
አብሔር ቸርነት በረከት ታገኛለህ፡ ዓዲ የዓውደ ዓመቱ
ቅዱስ ዮሐንስ ዕለት በሌሊት ውኃ ፯ ጊዜ ደግመህ ቤትህን
ብትረጭ ከዓመት ዓመት ሲሳይ ይገባልሃል። ዓዲ ወደ
ገበያ ዕቃ ለመግዛት ስትወጣ ፫ ጊዜ በትደግም ይቀናሃል።
ዓዲ ሌባ ነው ብለህ ለጠረጠርኸው ሰው በንብስት ላይ ጽፈህ
ብትሰጠውና ብታበላው የወሰደውን ይመልሳል ሰውነቱ ቢጠፋ
ብህ ሌብነት ያለበት ሰው ወሬውን ያወራልሃል ለሲሳይ መዝ፡
፺፭ የብቡ ለእግዚአብሔርን ከ፲፬ መዝሙር ጋር ጽፈህ በቤትህ
በ፬ ማዕዘን ብትሰቅል በእግዚአብሔር ቸርነት ሲሳይ ታገኛለህ።
ርግብና ዶሮ ለሚያረባ ሰው መዝ፡ ፷፮ እግዚአብሔር ይባርከነን
በልሙጥ ወረቀት ጽፎ በማደሪያቸው ማኖር ነው ይባረካሉ፡
ዳግም ለአትክልትና ለማንኛውም አዝርዕት በዕቃ ላይ ጽፎ
ጽሑፉን በሌሊት ውሃ አጥቦ ቢረጨት አዝመራው ይባረካል፡
ዘትሮው ነገር በድንነት ተጨንቆ ሲሳይ ባአጣ ሰው መዝ፡
፸፩ እግዚኦ ኵነኔከን በልሙጥ ወረቀት ጽፎ ፯ ጊዜ ደግሞ
በቤቱ በ፬ ማዕዘን ይለብጠው ፯ ቀን ድረስም ፩ ፩ ጊዜ
ይድገመው እግዚአብሔር ሲሳይ ያገለታል። ዓዲ በወሊድ

ለታመመች ሴት ወይወርድ ከመ ጠል ውስተ ፀምር እስከ ሚለው ድረስ በዕቃ ላይ ጽፈህ ጽሕፈቱን በሚጠጣ ነገር አጥበህ ፯ ጊዜ ደግመህ ብታጠጣት በእግዚአብሔር ቸርነት ትወልዳለች ዓዲ የርግብ ኵስ በእራሷ ላይ እያጤስህ ይህን መዝሙር ነገሥተ ተርሴስ እስከሚለው ድረስ ብትደግምላት በእግዚአብሔር ቸርነት ትወልዳለች ፡፡




ለወሊድ መዝ፡ ፻፲፪ ጥቀ ኀርጎ በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ ብታሲዛት በእግዚአብሔር ቸርነት ትወልዳለች ትወልዳለች ዓዲ ከማንኛውም ጭንቀት ለመዳንና በሰው ዘንድ ክብር ለማግኘት በሌሊት ውሃ ፯ ጊዜ ደግመህ ብትታጠብ ወይም በቅብዐ ቅዱስ ደግመህ በትቀባ በእግዚአብሔር ቸርነት የፈለከውን ነገር ታገኛለህ፡፡ ዓዲ ለራስ ፍልፀት መዝሙሩን ከጠልሰሞቹ ጋር በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ ብታሲዝ የታመመው ከበሽታው ይድናል፡ ዓዲ ለበረከት ከአውድማ ላይ እህሉ ሳይሰፈር ፫ ጊዜ ደግመህ እፈስ በእግዚአብሔር ቸርነት በረከት ታገኛለህ፡፡




ሰው ቀንቶ በተቆጨብህ ጊዜ ሥራይ ያደርግብኛል ብለህ ብትጠረጥር መዝ፡ ፸፫ ለምንት ገደፍከነ ፯ ጊዜ ደግመህ ሰውነትህን አማትበህ ብትሄድ ከክፉ ነገር ያድንሃል፡፡ ዓዲ ለራስ ፍልፀት በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ ብተይዝ ከበሽታህ ትፈወሳለህ፡፡ ዓዲ ለታሠረ ሰውም ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ ስጠው ይፈታል፡፡

ለታመመ ሰው መዝ፡ ፸፱ እግኒ ስለ እግዚአን በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፫ ጊዜ ደግመህ ብታሲዘው ይድናል። ዓዲ ጽሑፉን በዶሮ ማር አጥኖ ቢይዙት ከጠላት ያድናል።

የየኸውንና የሰማኸውን ለማጥናት ልቡናህ አስተዋይ እን ዲሆን መዝ፡ ፸፭ ተአውቀ እግዚአብሔር በይሁዳን በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ያዝ በሌሊት ውኃ ላይም ፫ ጊዜ ደግመህ ጠጣ። ዓዲ እንቅልፍ ለማይዘው ሰው በሌሊት ውኃ ፫ ጊዜ ደግመህ ብታጠጣው እንቅልፍ ይይዘዋል ከሽም ጋር ብትጣላ ከሹመ ቱም ላሽረው ብትል መዝ፡ ፸፮ ቃልየን የሌሊት ውኃ ቀድተህ እስከ ፫ ቀን ድረስ ፫ ፫ ጊዜ ደግመህ ከበሩ ላይ ድፋበት እስከ ፳ ቀን አይደርስም ጠልሰሞቹንም ከበሩ ቅበር ይሻራል።



ዓዲ ከቤትህ ሳትወጣ በዘይት ወይም በቅቤ ላይ ፫ ጊዜ ደግ መህ ተቀባ በእግዚአብሔር ቸርነት ከክፉ ነገር ይጠብቅሃል። ዓዲ ለታመመ ሰው በትኩስ እንጀራ የሰውየውን ፊት አብሰህ ለጥቁር ውሻ ስጥ ቢበላው ሰውዬው ይድናል ካልበላው ይሞታል



ለራዕይ መዝ፡ ፸፩ እጽምዑን ስትተኛ ፫ ቀን እየደገምህ ብትተኛ ያሰብከውን ነገር ሁሉ እራሱ ዳዊት መጥቶ ይነግርሃል። ሰው በመከራና በድህነት ቢወድቅ የሚበላውም ቢያጣ መዝ፡ ፸፱ ኖላዊሆሙን በየዕለቱ ፶ ፶ ጊዜ ቢደግም እግዚአብ ሔር ኀዘኑን ይሰማዋል የለመነውንም ይሰጠዋል ለመካን ሴት መዝ፡ ፹ ተፈሥሑን በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ለእሱ ግማ ሽ ግማሹን አሲዛት በሌሊት ውኃ ላይም ደግመህ

ሹን ለእሷ ብታጠጣት በእግዚአብሔር ቸርነት ታረግዛለች ዓዲ በሌሊት ውኃ ላይ ፯ ጊዜ ደግመህ ለአትክልት ብትረጨው ያፈራል ዓዲ ቁርጥማት ነቀርሳ ለሚያመው ሰው በወረቀት ጽፈህ ብታሲዘው ይድናል።

ለርግብና ለዶሮ እርባታ መዝ፡ ፻፫ ጥቀ ፍቁርን በልሙጥ ወረቀት ጽፈሕ ከቦታቸው ብታኖር ይረባሉ። ዓዲ ጠላት በተነሳብህ ጊዜ ከመቅደስ ደጃፍ እጅህን ዘርግተህ ከመዝሙር ፴ና ፱ ጋር ይህን መዝሙር ፫ ቀን ፫ ፫ ጊዜ ብትደግም እግዚአብሔር ጠላትህን እስከ ወር ያስታግስልሃል ዓዲ በንዳድ ለታመመ ሰው በ፫ የወይራ ቅጠል ፫ ጊዜ ደግመህ ብታበላው በእግዚአብሔር ቸርነት ይድናል።

ለጠላት ማስታገሻ መዝ፤ ፻፬ ተሠሃልከን እስከ ፲ ቀን ፲ ፲ ጊዜ ጠላትህን እያሰብክ ብትደግም እግዚአብሔር ያስታግስልሃል ዓዲ ከሹመትህ በተሸርክ ጊዜ ከመዝሙር ፻፱ ጋራ በጽጌረዳ አበባ ላይ ፯ ጊዜ ደግመህ ፊትህን ቀብተህ የሻረኽን ሰው ብትገናኘው ወደ ሹመትህ ይመልስህል። ዓዲ በሽታ በሀገር ቢነሳ በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ከቤትህ ደጃፍ ብትሰቅለው ከክፉ ነገር ይሠውርሃል። ዓዲ አንድ ሰው ታሞ እንደበቱ ቢንተባተብና ቢያነዝዘው በ፩ ኩባያ ውኃ ላይ መዝሙሩን ፯ ጊዜ ደግመህ አጠጣው የተረፈውን እፍስበት በእግዚአብሔር ቸርነት ይድናል።

ለክፉ ነገርና ለዓይነ ሰብእ መዝ፤ ፻፭ አፅምዕ እግዚኦን በልሙጥ ወረቀት ጽፎ ፫ ጊዜ ደግሞ ቢይዙ በእግዚአብሔር ቸርነት ያድናል። ዓዲ በከብትህ በሽታ ቢገባብህ በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፫ ጊዜ ደግመህ ነባር በሆነው ከብትህ ላይ እሠር እግዚአብሔር ሁሉንም ያድናልሃል።

ርግብና ዶሮ ለማያረባ ሰው መዝ፡ ፹፮ መሠረተቱሃን በልሙጥ ወረቀት ጽፎ በቤቱ ያኑር ይረባሉ። ዓዲ አዲስ ቦታ ስትቆረቁር የአትክልትም ቦታ ብታደርግ ጽፈህ ቅበር፡ ለጠላት ማስታገሻ መዝ፡ ፹፯ እግዚአብሔር አምላክ መድኃኒትየን ፫ ቀን ፫ ፫ ጊዜ ጧት ጧት ደግመህ የምትጠላውን ሰው ስም ከነእናቱ ብትጠራ እግዚአብሔር ያስታግስልሃል። ዓዲ ለታሠረ ሰው በሌሊት ውሃ ፫ ፫ ጊዜ እየደገምህ ብትሠጠው ይፈታል፡ ዓዲ ባል ለሌላት ሴት በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ የጽጌ ረዳ የቀጋ የእጋም አበባቸውን በውሃ አሽተህ ጨምቀህ በ፯ኛው ቀን በራሷ መዝሙሩን እስከ ፯ ቀን ፯ ፯ ጊዜ ደግመህ ትረብርበው ጽህፈቱንም በአንገቷ ትያዝ እግዚአብሔር የሚያገባትን ይሰጣታል ዓዲ ለኮበለለ ሰው እግረ መልስ በልሙጥ ወረቀት የኮበለለውን ሰው ስምና ዳዊቱን ጽፎ ፯ ጊዜ ደግሞ በዶሮ ማርና በዕጣን አጥኖ የተጻፈውን ወረቀት በሸንበቆ ጨምሮ ወደ ምሥራቅ ባለ መስኮት መስቀል ነው ይመለሳል። ዓዲ አዲስ ከብት ስትገዛ ወደ ቤትህ ከመግባትህ በፊት መዝ፡ ፺፰ ምሕረትከን ፯ ጊዜ በውኃ ደግመህ እርጨው ዓዲ ለሀብት ለሲሳይ ማግኛ ፴ ቀን በጥርኝ ውሃ ፯ ፯ ጊዜ ደግመህየበየትህን ዙሪያውን እርጭ ሲሳይ ታገኛለህ፡ ዓዲ ሰውን ወደ አንተ ለመምጣት ብትፈልግ በሌሊት ውኃ ፯ ጊዜ ደግመመህ የደጅህን ዙሪያውን እርጨው ሲሳይ ይዞ ይመጣልሃል። መዝ፡ ፺፱ እግዚአ ጸወነ ኮንከነን ዘወትር ፫ ፫ ጊዜ ቢደግሙት እግዚአብሔር ኃጢአትን ያስተሥርያል። መዝ፡ ፺ ዘኃድርን በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ብትይዝ ሌሊት በምትንቀሳቀስበት ጊዜ ከአጋንንትም ሆነ ከአራዊት ፍርሃት ትድናለህ። ዓዲ ለሕፃንና ለአረጋዊ በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመመህ ብታሲዝ ይድናሉ። ያሰውን ነገር ከፉም ሆነ ደግ እንዳገለጥልህ ብትወድ መዝ፡ ፺፩ ይሄይስን ከመዝሙር ፹ ጋራ ወደ ሜዳ

(መስከ) ሄደህ ንጭ ዕጣን በአፍህ ይዘህ ፯ ጊዜ ብትደግም እግዚአብሔር በራዕይ ይገልጥልሃል፡ ዓዲ በቤትህ በ፬ቱ ማዕዘን ጽፈህ ብትሰቅል ለአትክልትም እንዲሁ ብታደርግ ከዓመት እስከ ዓመት እግዚአብሔር ረድኤት ይሰጥሃል። ዓዲ ለበሽተኛ በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ ብትሰጠው ይፈወሳል፡

በመርከብ ስትሄድ የማዕበል ንፋስ በነሣብህ መዝ፤ ፺፪ እግዚአብሔር ነግሠ በ፩ ዕቃ ውኃ ምልተህ መዝሙሩን ፯ ጊዜ ደግመህ ምራቅህን ትፋበት ከዚህ በኋላ መርከቡን እርጭ የተረፈውን ከነዕቃው ከባሕሩ ጣለው እግዚአብሔር ከጥፋት ያድንሃል፡

ከምትፈራው ቦታ መዝ፤ ፺፫ እግዚአብሔር እግዚአነ ዘወትር ፩ ፩ ጊዜ ብትደግም ከሌባም ሆነ ከአራዊት ከማንኛውም ክፉ ነገር በእግዚአብሔር ቸርነት ትድናለህ።

ጠላትህ ሊያጠፋህ ቢፈልግህ መዝ፡ ፺፬ ንዑ ንትፈሣሀን ከመዝሙር ፺፭ ጋራ ስትተኛ ፫ ፫ ጊዜ ብትደግመው ጠላትህ ይታገስልሃል። ዓዲ በድኩላ ብራና ጽፈህ ብትይዘው ጋኔን የያዘው ሰው ለፍልፎ ጋኔኑ ይለቀዋል ያጠናውን ለሚረሳ መዝ፡ ፺፭ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲሰ ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ ብታሲዘው ይረዳዋል ዓዲ አዲስ ቦታ ለልማት ብታስብ ፯ ጊዜ ደግመህ እርጨው ከክፉ ይጠብቅልሃል።

ሰው ሆዱን ሆነ እባጭም ቢታመም መዝ፡ ፺፮ እግዚአብሔር ነግሠ ትትሐሠይ ምድርን በዕቃ ላይ ጽፈህ በውኃ አጥበህ መዝሙሩን ፯ ጊዜ ደግመህ ለበሽተኛው አጠጣው በእግዚአብሔር ቸርነት ይድናል።

እዕዋፍ፡ ዘርህን እንዳይለቅሙት መዝ፡ ፺፯ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲሰ በድኩላ ብራና ጽፈህ በረጅም ሸንበቆ ከዘሩ መካከል ስቀለው አይነኩብህም ዓዲ ክፉ ሕልም ዘወትር

ለሚያቃዠው ሰው መዝሙሩን በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ ዕጣን አጥነህ አሲዘው በእግዚአብሔር ቸርነት ይድናል
ማደሪያ ላጣ ሰው መዝ፡ ፺፰ እግዚአብሔር ነግሠ ደንግፁ አሕዛብን በንጹሕ ሆነህ በጽጌ ረዳ ቅባት ፳፩ ቀን ፳፩ ፳፩ ጊዜ ደግመህ ቅባቱን አትረህ እየተቀባህ ውጣ ሀብት ይሰጥሃል። ለሰውም እንዲሁ ብታደርግለት ይሆናል።
መዝ፡ ፺፱ የብቡ ለእግዚአብሔርን በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ዘወትር ፯ ቀን ፯ ፯ ጊዜ ደግመህ ብትይዝ ሁል ጊዜ ደስተኛ ሆነህ ትኖራለህ። ብዙ መጠጣት ስትፈልግ መዝ፡ ፻፭ ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ኄርን ከመጠጣትህ በፊት በመጀመሪያ ፯ ጊዜ ደግመህ ብትጠጣ አትሰክርም።



ለዘኢያገድፍ መዝ፡ ፻፯ ጥቡዕ ልብየን በ፯ቱ ቀለማት በዕቃ ላይ ጽፈህ ከነጠልሰሙ የጻፍሕበትን ዕቃ በውድ ሙስተካ ዕጣንና በውርበርዴ ዕጣን አጥነህ አረቄ ምላው ከዚያ ላይ አንድ ወቄት ንጥር ማር ጨምረህ ንጹሕ ሆነህ ፯ ቀን መዝሙሩን ፯ ፯ ጊዜ ደግመህ ጠዋትና ማታ እየቀመስህ ተኛ የለማኸውን ነገር ታጠናለህ ማጥኛነቱ እጅግ ፍቱን ነው።



ጠላትህን ለማስታገስ ብትፈልግ መዝ፡ ፻፰ እግዚኦ ኢትእመመኒን ወይጥፋዕ እምድር ዝክሩ እስከሚለው ድረስ

በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ ከቦታው ቅበር ይታገስልሃል። **ዓዲ ባልተተከሰ** ሸክላ ጽፈህ ጠላቶቼን እነ ዕገሌን እንደዚህ ቅበር ብለህ ቅበረው ጠላቶችህ ይታገሳሉ ይህ በጣም ፍቱን ነው። ስትጽፍ ከቤትህ አትጻፈው ከሜዳ ጻፈው። ዓዲ ቅዳሜ ቀን በጥርኝ ለናፍጭ ላይ ፫ ጊዜ ደግመህ በጠላትህ ቤት እርጨው ጠላትህ ከነቤተሰቡ ይታገስልሃል። ዓዲ ቅዳሜ ቀን በሐዲስ ሸክላ በጠዋት ውኃ ከመጥረጊያው ሣዕር አንስተህ በዚያ ብዕር ጽፈህ ጽፈቱን በውኃው አጥበህ በጠላትህ ቦታ ፀሐይ ሳይወጣ እርጨው በእግዚአብሔር ቸርነት ይታገስልሃል፡ **ከብት ቢጠፋብህ መዝ፡ ፻፲፩ ብፁዕ ብእሲ ዘይፈርሆን** የምትጠረጥረውን ሰው ሁሉ ስም በወረቀት ጽፈህ በሸክላ ጭቃ እየጠቀለልህ አንድ ባዶ ወረቀት ጨምረህ በውኃ ላይ አድርገህ መዝሙሩን ፫ ጊዜ ደግመህ መጀመሪያ የወጣውን እይ ሌባው እሱ ነው **ስተቀበረ ነገር ማውጫ መዝ፡ ፻፲፫ እመ ይወጽኡን** በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፳ ጣት ባለው ነጭ ዶሮ በአንገቱ እሠርለት ከማንም ስፍራ የተቀበረ ቢጠፋብህ ዶሮውን ስደደው ሮጦ ይቆምበትና የመብላት ምልክት ካሳየበት ቦታ ይገኛል ለተሠረቀም ቢሆን ንብረትህ ካለበት ቦታ ይመራል **ለልቃሻ ለሆነ ሕፃን መዝ፡ ፻፲፬ አፍቀርኩን** በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፫ ጊዜ ደግመህ እሠርለት ከማልቀሱ ይቀንሳል **ጠላትህ ያለ አግባብ ከዳኛ ፊት ቢያቆምህ መዝ፡ ፻፲፭ አመንኩን** የባላጋራህንና የዳኛውንም ስም ጠርተህ ደግመህ ሂደህ ግጠም በእግዚአብሔር ቸርነት ድል ታደርጋለህ። **ሕግ ማድረስ ለጠመመው ሙሽራ መዝ፡ ፻፲፯ ግነዩ ለእግዚአብሔርን** በጠርሙስ ላይ ጽፈህ የዕገሊትን ልጅ የዕገሌን ብልቱን ፍታ ብለህ ሙስተካ አጥነህ አጠጣ በእግዚአብሔር ቸርነት ይፈታለታል።

ከሹመትህ እንዳትሻር መዝ፡ ፻፲፰ አሌፍን ንጹሐ ሆነህ ፲፰ ጊዜ ብትደግም ከሹመትህ አትሻርም።

ከንገሥታትና ከመኳንንት ቤት ስትገባ መዝ፡ ፻፳ አንሣ ዕሩን ጽፈህ ፫ ጊዜ ደግመህ ብትይዝ ክብር ታገኛለህ።

ወላትህ ከሶህ ከዳኛ ፊት ቢወስድህ መዝ፡ ፻፳፩ ተፈሣሕኩን መናብረተ ቤተ ዳዊት እስከሚለው በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፯ ጊዜ ደግመህ ያዝ በእግዚአብሔር ቸርነት የተቃና ፍርድ ታገኛለህ። ዓዲ ከቧላ ለተጣላች ሴት ውሃ ባልነካው ቅቤ ፯ ጊዜ ደግመህ ስጣት ተቀብታ ትውጣ ከባሏ ጋር ትታረቃለች፡

በኀዘን ችግር ለተጨነቀ ሰው መዝ፡ ፻፳፪ ኀቤከ እግዚኦን ፫ ጊዜ ቢደግም ከኀዘኑ ይረጋጋል ከሚፈራው ያድነዋል

በተቅማጥ ለተያዘ ሰው መዝ፡ ፻፳፫ ሶቦ አኮን በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፫ ጊዜ ደግመህ በቀኝ ክንዱ ብታሥርለት በእግዚአብሔር ቸርነት ይድናል።

ዘወትር ከባሏ ጋር ለምትጣላ ሴት መዝ፡ ፻፳፬ እለ ተወከሉን በልሙጥ ወረቀት ጽፈህ ፫ ጊዜ ደግመህ አስይዛት ሰላማዊ ትሆናለች።

ዘር በምትዘራበት ጊዜ መዝ፡ ፻፳፭ አመ ሜጠን በዘሩ ላይ ፯ ጊዜ ደግመህ ብትዘራ በእግዚአብሔር ቸርነት አዝመራው ጥሩ ሆኖ በቅሎ ይባረክልሃል።

ለዕደ ጥበብም ሆነ ለሁሉም ነገር የቀንጠፋ ተቀጽላ ከምሥር ወጥ ጋር ሠርተህ ፌ መንክርን ፯ ጊዜ ደግመህ ብላ

ለሙግት አፍ እንዳተባ ድንብላል ነጭ ሽንኩርት የጽጌ ረዳ ሥሩንና አበባውን የምሥርች ሥር ቁንዶ በርበሬ አሞሌ ጨው ዝንጅብል ጥቁር አዝሙድ አንድ ላይ ሰልቆ በሸንብራ ቂጣ ጋግሮ ከዳዊት መሠረታቲሃንና ዓቢይን ፯ ፯ ጊዜ ደግሞ ፯ ቀን በባዶ ሆድ ቢበሉት ለሙግትም ሆነ ለቃለ እግዚአብሔር ይሆናል ማሳሰቢያ በጠልሰመ ዙሪያ ያለው ሐረግ አይጸፍም ።